# የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## ለውጭ አገር ዜጎች
## የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን
## ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 44/2013

## 1. የመመሪያው አስፈላጊነት

ተገቢው እውቀትና ክህሎት ያላቸው የውጭ አገር ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ በዜጎች ሊሸፈኑ በማይችሉ የሙያ መስኮች እና በአመራር ደረጃ በመሰማራት ተተኪ ኢትዮጵያዊያንን የሚያፈሩበትና ለሀገሪቱ የእውቀትና የቴኮኖሎጂ ሽግግር አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች በተፈቀደላቸው የሥራ መስኮችና ድርጅቶች ውስጥ ሕግና ሥርዓትን ተከትለው እየሰሩ መሆኑን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት የተጠናከረ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሚኒስቴሩ ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ጥር 2002 ዓ.ም አውጥቶ በሥራ ላይ ያለውን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

## 2. አውጪው ባለሥልጣን

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 170(1)(ሠ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ጥር 2002 ዓ.ም አውጥቶ በሥራ ላይ ያዋለው መመሪያ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

## 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 44/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 4. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ “አሠሪ” ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2(1) ያለው ትርጉም

ይኖረዋል፡፡ 2/ “ሚኒስቴር” ማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡

3/ “የውጭ አገር ዜጋ” ማለት የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

4/ “አግባብ ያለው ባለሥልጣን” ማለት በየክልሉ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህጎችን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው።

5/ “ተገቢ ሙያ” ማለት የውጭ አገር ዜጋው ለሚቀጠርበት የሥራ መደብ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰጠው ሕጋዊ የትምህርትና ሥልጠና ማስረጃ ወይም የሥራ ልምድ ማለት ነው።

6/ “ተተኪ ሠራተኛ” ማለት የውጭ አገር ዜጋው በተመደበበት የሥራ መደብ ላይ በረዳትነት ተመድቦ የውጭ አገር ዜጋውን ለመተካት ዕውቀት የሚቀስም ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ማለት ነው።

7/ "የሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት” ማለት እንደጉዳዩ አግባብነት ወደ አገር ውስጥ ገብተው ለመሥራት የሥራ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ለሚቀርብላቸው የውጭ አገር ዜጎች የድጋፍ ደብዳቤ ወይም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥ አካል ነው።

8/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው።

9/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትም ጾታ ያካትታል።

## 5. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጎች፣ በቀጣሪ ድርጅቶችና፣መመሪያውን በሚያስፈጽሙ የመንግሥት አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 6. <u>የሥራ ፈቃድ ማውጣት ስለማስፈለጉ</u>

1/ በኢትዮጵያዊያን ሊሸፈን በማይችል የሥራ መስክ ላይ የውጭ አገር ዜጎችን ቀጥሮ ለማሰራት የሚፈልግ አሠሪ ከሚኒስቴሩ ወይም ሕጋዊ ውክልና ከተሰጠው አካል የሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን በድርጅቱ ውስጥ ለመቅጠር ሲጠይቅ ብቻ ነው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው የሥራ ፈቃድ የሚያገለግለው ፈቃዱን በጠየቀው አሠሪ ድርጅት ውስጥ ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መደብ ላይ ለመሥራት ብቻ ነው።

## 7. <u>የሥራ ፈቃድ ማውጣት የማያስፈልጋቸው የውጭ አገር ዜጎች</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት የውጭ አገር ዜጎች፡-

1/ የኢትዮጵያ ተወላጅ ሆነው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዙ የውጭ ዜጎች፣

2/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚያረጋግጠው መሠረት፡-

ሀ/ የዲፕሎማቲክ ሚሽን አባሎች፣

ለ/ የቆንስላ አባሎች፣

ሐ/ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች፣

መ/ የአፍሪካ ሕብረት አባሎች፣

ረ/ የዓለም ባንክ አባሎች፣

ሰ/ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባሎች፣

ሸ/ የዓለም አቀፍ አቶሚክ ኃይል ወኪል አባሎች እና

ቀ/ ሌሎች ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ድርጅቶች አባሎች፣

የሥራ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የውጭ አገር ዜጋ በተለየ ሁኔታ የሚቀጠር ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት አሠሪው የሥራ ፈቃድ ሊያወጣለት ይገባል።

## 8. <u>የሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎች</u>

ማንኛውም አሠሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋን ቀጥሮ ለማሰራት የሥራ ፈቃድ ማውጣት የሚችለው፤

1/ የውጭ አገር ዜጋው እንዲቀጠርበት የተጠየቀው የሥራ መስክ በኢትዮጵያዊያን ሊሸፈን የማይችል መሆኑን አግባብነት ያለው ሴክተር መ/ቤት በሚሰጠው የድጋፍ ደብዳቤ ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ፣

2/ የውጭ አገር ዜጋው በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ በዕርዳታ መልክ ወይም በበጎ ፈቃድ የትምህርት፣ የጤና እና ተያያዥነት ያላቸው ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የተሰማራ ሆኖ አገልግሎቱም ለሀገሪቱ ጠቃሚና ተፈላጊነት ሲኖረው፣

3/ ዋና መሥሪያ ቤቱ ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነውን ድርጅት ወክሎ ተቀማጭነቱን በኢትዮጵያ ውስጥ በማድረግ የሚሠራ የውጭ አገር ዜጋ (የንግድ እንደራሴ) ሲሆን፣

4/ የውጭ አገር ዜጋው በሽርክና ወይም በአክሲዮን በተቋቋመ ድርጅት ውስጥ አባል ከሆነ ወይም ድርሻ ካለው እና በዚሁ ድርጅት ውስጥ በደመወዝ ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን፣

5/ የውጭ አገር ዜጋው መንግሥት ባደረገው የሁለትዮሽ ወይም የብዙ ወገን ስምምነቶች ወይም ውሎች መሠረት ሲቀጠር፣

6/ አሠሪው/የውጭ ባለሀብት ብቻውንም ሆነ ከአገር ውስጥ አሠሪ/ባለሀብት ጋር በቅንጅት ላቋቋመው ድርጅት ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን ለመቅጠር ሲፈልግ፣

7/ ለማሽን ተከላ ወይም ለኮሚሽንግ ሥራ የሚመጣ የውጭ አገር ዜጋ፣

8/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚያረጋግጠው መሠረት ከኢትዮጵያ ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት ያላቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የዲፕሎማቲክ አባላት ጥገኞች፣

9/ ከኢትዮጵያዊያን ጋር በጋብቻ የተሳሰሩና ነዋሪነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች፣

10/ አሠሪው/የአገር ውስጥ ባለሀብት ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ ከውጭ ኢንተርፕራይዝ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት የውጭ አገር ዜጋው ለሥራው አስፈላጊ መሆኑን በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሲረጋገጥ የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

11/ በዚህ አንቀፅ የተመለከቱት ቢኖሩም በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 በአንቀጽ 37(3) በተደነገገው መሠረት የውጭ ባለሀብት ለሚያካሂደው ድርጅት የውጭ ዜግነት ያላቸውን ከፍተኛ ማኔጅመንት አባላት ለመቅጠር ገደብ አይደረግበትም፡፡

## 9. ስለ ሥራ ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ

1/ የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ቀጣሪ ድርጅት ብቻ ነው፡፡

2/ ማንኛውም አሠሪ የውጭ አገር ዜጋ ለመቅጠር የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገው የማመልከቻ ቅጽ የሚጠይቀውን መረጃ በማሟላት ነው፡፡

3/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 (2፣3፣4 እና 6) እንዲሁም ቀጣይነት በሌላቸው እንደ መሣሪያ ተከላ፣ ሱፐርቪዥን፣ የኦዲትና የሂሳብ ሥራ ላይ ከሚቀጠሩት በስተቀር በሌሎች የሥራ መደቦች ለሚቀጠር የውጭ አገር ዜጋ ተተኪ ኢትዮጵያዊ መመደቡን ወይም መቀጠሩን የሚገልጽ ማስረጃ በአሠሪው ይቀርባል፡፡

4/ አሠሪው ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ስለሚሰጠው የዕውቀት ሽግግር ፕሮግራምና ስለሚተኩበት የጊዜ ገደብ በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

5/ አሠሪው በጤናና በትምህርት ዘርፍ የሚቀጠሩ የውጭ አገር ዜጎችን በተመለከተ አግባብ ባለው የመንግሥት መ/ቤት የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያቀርባል፡፡

## 10. ተተኪ ኢትዮጵያዊያንን ስለማሰልጠን

1/ አሠሪው የሥራ ፈቃድ በተሰጠበት የጊዜ ገደብ ውስጥ የውጭ አገር ዜጎችን የሚተኩ ኢትዮጵያዊያን እንዲሰለጥኑ በማድረግ ሪፖርት በየ6 ወር ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ስለተተኪው ኢትዮጵያዊ አጠቃላይ የዕውቀት ሽግግርና የሥራ ሁኔታ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

## 11. በመንግሥት አካላት ስለሚሰጥ ማረጋገጫ ወይም የድጋፍ ደብዳቤ

1/ አሠሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2) መሠረት የሥራ ፈቃድ የሚጠየቅለት የውጭ አገር ዜጋ ስለሚሰራው ሥራ ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ጠቀሜታ እና የውጭ ዜጋው እንዲቀጠርበት የተጠየቀው የሥራ መስክ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(1) በተደነገገው መሠረት በኢትዮጵያዊያን ሊሸፈን የማይችል ስለመሆኑ አግባብ ካለው የመንግሥት መ/ቤት የተሰጠ የጽሑፍ ማረጋገጫ ወይም የድጋፍ ደብዳቤ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም አንዳንድ ድርጅቶች በሥራቸው ባህሪ ምክንያት ከመንግሥት መ/ቤቶች ተገቢውን ማረጋገጫ ወይም የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የማይችሉ መሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ እና የውጭ አገር ዜጋው ለተጠየቀው የሙያ መስክ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የተመለከቱት ሌሎች መሥፈርቶች ሲሟሉ የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

## 12. የሥራ ፈቃድ የጊዜ ገደብና ዕድሳት

1/ የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው በአንድ የሥራ መደብ ላይ ለመሥራት እስከ ሦስት ዓመት ሲሆን፣በየዓመቱ ይታደሳል። ሆኖም ሚኒስቴሩ የሦስት ዓመቱን የጊዜ ገደብ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል።

2/ የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ የቀረበበት ምክንያት በቂ ሆኖ ካልተገኘ ሚኒስቴሩ የሥራ ፈቃዱን ላያድስ ይችላል።

3/ የሥራ ፈቃድ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋን ቀጥሮ ለማሰራት ካመለከበት ቀን ጀምሮ ነው።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የውጭ አገር ዜጋው አገር ውስጥ ከገባ 90 የሥራ ቀናት በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም።

## 13. የአሠሪ ግዴታዎች

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ያሉት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አሠሪው የሚከተሉት ተጨማሪ ግዴታዎች ይኖሩበታል።

1/ የሥራ ፈቃድ የተሰጠውን የውጭ ዜጋ በተፈቀደለት የሙያ መስክ ላይ ብቻ የማሰራት፣

2/ ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋው ከሥራ ቦታ ከተሰወረ ሠራተኛው መጥፋቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ የማሳወቅ፣

3/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው የውጭ አገር ዜጋው በአካል እንዲቀርብለት ሲጠይቅ አስፈላጊውን የመፈፀም፣

4/ አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን አገልግሎት የማይፈልግ ሆኖ የሥራ ውሉን ሲያቋርጥ የሥራ ውሉን ባቋረጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ በማሳወቅ የሥራ ፈቃድ ደብተሩን የመመለስ፣

5/ የውጭ አገር ዜጋው የሚሠራበትን የሥራ ቦታ ከቀየረ አዲሱን አድራሻ፣አድራሻው ከተቀየረበት ቀን ጀምሮ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፣

6/ ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የአገሪቱን ሕጎች መጣሱ ሲረጋገጥ ወዲያውኑ የሥራ ፈቃዱን ለሚኒስቴሩ አቅርቦ እንዲሰረዝ የማድረግ፣

7/ የሥራ ፈቃድ የሌለውን የውጭ አገር ዜጋ በሥራ ላይ ያለማሰማራት፣

8/ የውጭ አገር ዜጋውን የመኖሪያ አድራሻ መዝግቦ በመያዝ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የማሳየት/የማቅረብ፣

9/ የውጭ አገር ዜጋውን በሕገወጥ ሥራዎችና በሌላ ለሞራል ተጻራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ ያለማሰማራት፣

10/ ከተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ ለተተኪ አትዮጵያዊያን ተገቢው እወቀትና ክህሎት የሚተላለፍበትን ሁኔታ የመፍጠርና የማረጋገጥ፡፡

## 14. <u>የተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ ግዴታዎች</u>

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ያሉት የሠራተኛው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

1/ በሥራ ፈቃድ ደብተሩ ላይ ለተመለከተው አሠሪ አሠሪ ብቻ የመሥራት፣

2/ የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ በመያዝ በሥራ ገበታው ላይ የመገኘት፣

3/ በሥራ ፈቃድ ደብተሩ ላይ በተመዘገበው የሥራ መደብ /ሙያ ላይ ብቻ የመሰማራት፣

4/ ለተተኪው ኢትዮጵያዊያን እውቀት የማስተላለፍ፣

5/ በሕገወጥ ሥራዎችና በሌላ ለሞራል ተፃራሪ በሆኑ ተግባራት/ሥራዎች ላይ ያለመሰማራት፣

6/ የውጭ አገር ዜጋው ወደ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በመቅረብ ሪፖርት እንዲያደርግ በሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው ሲጠየቅ በወቅቱ የመቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 15. <u>አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ያለባቸው መሥፈርቶች</u>

1/ ማንኛውም አሠሪ ለሚቀጥረው የውጭ አገር ዜጋ አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ በቀጣሪ ድርጅት የሚቀርብ የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ፣

ለ/ የተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የግል ታሪክ የተሞላበት ቅጽ፣

ሐ/ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የውጭ አገር ዜጋው የትምህርት ማስረጃ እንዲሁም የሥራ ልምድ ማስረጃ /ኦሪጅናልና ኮፒ/፣

መ/ የውጭ አገር ዜጋው ከሦስት ወራት ያላነሰ ጊዜ ያለው የጉዞ ሕጋዊ ፓስፖርት፣

ሠ/ የፓስፖርት መጠን ያላቸው የውጭ አገር ዜጋው አራት ጉርድ ፎቶግራፎች፣

ረ/ እንደአግባቡ ጊዜው ያላለፈበት የቢዝነስ ቪዛ (BV)፣ የሥራ ቪዛ (WV)፣ ለመንግሥት ተቋማት የሚሰጥ ቪዛ (GV) ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት የሚሰጥ ቢዛ (NV)፣

ሰ/ አግባብነት ካለው የመንግሥት መ/ቤት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣ በተለይ የውጭ አገር ዜጋው በጤና ወይም በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ እንደአግባቡ ከጤና ወይም ከትምህርት ተቋማት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ሸ/ እንደአግባቡ የውጭ አገር ዜጋው ከአሠሪው ጋር የገባው የሥራ ቅጥር ውል፣

ቀ/ በሕግ የተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፣

2/ አሠሪው የግል ድርጅት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት በተጨማሪ እንደአግባቡ የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማቅረብ አለበት፣

3/ አሠሪው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 ከተመለከቱት በተጨማሪ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ምዝገባ ኤጀንሲ የተሰጠ የምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ አለበት፣

4/ አሠሪው የሃይማኖት ተቋም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት በተጨማሪ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ የምዝገባ ሠርተፊኬት ማቅረብ አለበት፣

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ የተመለከተው ቢኖርም የውጭ አገር ዜጋው የትምህርት ማስረጃ ከሌለውና የሚመለከተው የመንግሥት አካል ባለው የሥራ ልምድ መሠረት ሥራውን መሥራት እንደሚችል ገልጾ ድጋፍ ከሰጠው ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

6/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1/ረ የተመለከተው ቢኖርም፡-

ሀ/ በኢትዮጵያና በውጭ ዜጋው አገር መካከል ቪዛ ያለመጠየቅ ስምምነት

ካለ፣ ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8 እና 9 ለተመለከቱት፣

አሠሪው ቪዛ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡

## 16. የሥራ ፈቃድ ለማደስ መሟላት ያለባቸው መሥፈርቶች

1/ ማንኛውም አሠሪ የሥራ ፈቃድ ለማደስ የሥራ ፈቃድ ጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን በማሟላት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የውጭ አገር ዜጋው የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻ፣

ለ/ የውጭ አገር ዜጋው ከሦስት ወራት ጊዜ ያላነሰ ጊዜ ያለው

ፓስፖርት፣ ሐ/ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ደብተር፣

መ/ የመኖሪያ ፈቃድ፣

ሠ/ አግባብነት ካለው የመንግሥት አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣ በተለይ የውጭ አገር ዜጋው በጤና ወይም በትምህርት ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ እንደአግባቡ ከጤና ወይም ከትምህርት ተቋማት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ረ/ እንዳግባቡ የውጭ አገር ዜጋው ከአሠሪው ጋር የገባው የሥራ ቅጥር ውል፣

ሰ/ የተተኪ ኢትዮጵያዊያንን የዕውቀት ሽግግር ሁኔታን የሚገልጽ

ሪፖርት፣ ሸ/ በሕግ የተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡

2/ አሠሪው የግል ድርጅት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት በተጨማሪ የታደሰ የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማቅረብ አለበት፤

3/ አሠሪው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት በተጨማሪ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተሰጠ የምዝገባ ሠርተፊኬት ማቅረብ አለበት፣

4/ አሠሪው የሃይማኖት ተቋም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት በተጨማሪ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ የምዝገባ ሠርተፊኬት ማቅረብ አለበት፡፡

5/ አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን የሥራ ፈቃድ በወቅቱ ሳያሳድስ የቀረ እንደሆነ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃበት በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ለመጀመሪያው ወር የዕድሳት ክፍያውን ሃምሣ በመቶ (50%)፣ ለሁለተኛው ወር ሰባ አምስት በመቶ (75%) እና ለሦስተኛው ወር መቶ በመቶ (100%) ቅጣት በተጨማሪ በመክፈል የሥራ ፈቃዱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡

## 17. የሥራ ፈቃድ ሊራዘም ስለሚችልበት ሁኔታ

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሥራ ፈቃድ ሊራዘም የሚችለው፡-

ሀ/ ተተኪው ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋውን የሥራ መደብ መሸፈን ሳይችል ሲቀር፣ ወይም

ለ/ የውጭ አገር ዜጋው ለሥራው አስፈላጊ ሲሆን እና የተቀጠረበትም ሥራ ቀጣይና አስፈላጊ መሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም፣ አሠሪው/የውጭ ባለሀብት ብቻውንም ሆነ በቅንጅት ለሚያካሄደው ድርጅት የውጭ ዜግነት ያላቸውን ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት የሥራ ፈቃድ ለማራዘም ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8(11) በተደነገገው መሠረት ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## 18. የሥራ ፈቃድ ደብተር ስለመተካት

1/ የሥራ ፈቃድ ደብተር ሲጠፋ አሰሪው ደብተሩ መጥፋቱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ደብተሩ የጠፋበትን ምክንያት የሚገልጽ በድርጅቱ የተፈረመ መግለጫ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ አሠሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተገለጸው በተጨማሪ የሥራ ፈቃድ ደብተር ለመጥፋቱ የፖሊስ ማስረጃ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ የቀረበውን ማስረጃ በማረጋገጥ እና በሕግ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምትክ የሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 19. የሥራ ፈቃድ ክሊራንስ

1/ ማንኛውም አሠሪ የሥራ ፈቃድ ላወጣለት የውጭ አገር ዜጋ ክሊራንስ ሲፈልግ የሚከተሉትን አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ከቀጣሪው ድርጅት የሚቀርብ የክሊራንስ ጥያቄ ማመልከቻ፣ እና

ለ/ ተመላሽ የሚደረግ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የውጭ አገር ዜጋው የሥራ ፈቃድ ደብተር፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም፣ ቀጣሪው ድርጅት በተለያዩ ምክንያቶች ከተዘጋ ወይም ሥራውን ካቆመ የውጭ አገር አገር ዜጋው ድርጅቱ ስለመዘጋቱ ወይም ሥራውን ስለማቆሙ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ማስረጃ በማቅረብ ሲጠይቅ የሥራ ፈቃድ ክሊራንስ ሊሰጠው ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ቀደም ብሎ የተሰጠው የሥራ ፈቃድ ጊዜው ካለፈ ከአንድ ወር በኋላ የሚቀርብ የክሊራንስ ጥያቄ የሥራ ፈቃዱ ያልታደሰበትን ጊዜ የሚሸፍን የእድሳት ክፍያን መጠን በመክፈል ክሊራንስ ማግኘት ይችላል፡፡

## 20. የሥራ ፈቃድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

1/ የሥራ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ይሠረዛል፡፡

ሀ/ የውጭ አገር ዜጋው የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ከጨረሰ በኋላ ለሥራው አስፈላጊ አለመሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ፣

ለ/ የውጭ አገር ዜጋው የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ የጊዜ ወሰን ባይጨርስም ለሥራው አስፈላጊ አለመሆኑ በአሠሪው ወይም በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የውጭ አገር ዜጋው ፈቃድ በተጠየቀለትና በተፈቀደለት ሥራ ላይ ሳይሆን በሌላ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲገኝ፣

መ/ የውጭ አገር ዜጋው ሲሰራው የነበረው ሥራ ሲያልቅ ወይም የማያስፈልግ ሲሆን ወይም ድርጅቱ ሲዘጋ፣

ሠ/ የሥራ ፈቃድ ከሦስት ወር በላይ ሳይታደስ ሲቀር፣

ረ/ የውጭ አገር ዜጋው በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ለአገሪቱ ደህንነት አስጊ መሆኑ አግባብ ባላቸው የመንግሥት አካላት ሲረጋገጥ፣

ሰ/ የውጭ አገር ዜጋው ሥራውን ሲለቅ፣

ሸ/ የሥራ ፈቃዱ የተገኘው በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ከሆነ፣

ቀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 እና 14 የተጠቀሱት የአሠሪና የሠራተኛ ግዴታዎች ሳይፈጸሙ ሲቀሩ፡፡

2/ የሥራ ፈቃድ ሲሰረዝ አሠሪው የሥራ ፈቃድ ደብተሩን ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት፡፡

## 21. በውጭ አገር ዜጎች ላይ ስለሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር

የውጭ አገር ዜጎችን አስመልክቶ በአዋጁ የተደነገጉና አዋጁን መሠረት በማድርግ የወጣ ደንብና መመሪያ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ እንደአግባቡ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

## 22. ጉዳይ አስፈፃሚ ስለመወከል

1/ ማንኛውም አሠሪ የውጭ አገር ዜጎችን ቀጥሮ ለማሰራት የሚያቀርበውን የሥራ ፈቃድ ጥያቄ የሚያስፈጽም ሰው መወከል አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወከል ጉዳይ አስፈጻሚ፡-

ሀ/ የድርጅቱ ሠራተኛ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የድርጅቱ መታወቂያ እና የቀበሌ መታወቂያ /ኦሪጅናል እና ፎቶ ኮፒ/፣

ለ/ ሦስተኛ ወገን ከሆነ በኢፌዲሪ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ የተረጋገጠ ውክልና እና የቀበሌ መታወቂያ፣

ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከቱት ቢኖሩም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሥራ ፈቃድ ጥያቄውን ራሱ ሊያስፈጽም ይችላል፡፡

**23. ስለ አገልግሎት ክፍያ**

የውጭአገር ዜጎችን ቀጥሮ ለማሰራት የሚፈልግ ማንኛውም አሰሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሥራ

ፈቃድ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያን በተማከተ ባወጣውደንብ ቁጥር 394/2009 መሠረት የሚከተለውን የአገልግሎት ክፍያ ሚፈጸምአለበት፤

1/ አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት ብር 2000.00 (ሁለት ሺ ብር)፣

2/ የሥራ ፈቃድ ለማሳደስ ብር 1500.00 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር)፣

3/ የሥራ ፈቃድ ደብተር ለመተካት ብር 1200.00 (አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር)፡ ፡

**24. ቅጣት**

1/ አሠሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተማከቱትን ግዴታዎችና ሌሎች ኃላፊነቶች ካልተወጣ

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በሌሎች አግባብነት ባላቸውሕጎች ስለቅጣት የተማከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚይሆኑበታል፡ ፡

2/ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ስለቅጣት የተማከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይምአግባብ ያለውባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው የሚሰራ የውጭአገር ዜጋ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል፡ ፡

**25. የመተግበር ግዴታ**

ማንኛውምሰውለዚህ መመሪያ አፈጻጸምየመተባበር ግዴታ አለበት፡ ፡

**26. የተሻረ መመሪያ**

ለውጭአገር ዜጎች የሥራ ፈቃድየሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ ጥር 30 ቀን 2002 ዓ.ምየወጣውመመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡ ፡

**27. የማሻጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተሰጠየሥራ ፈቃድ በዚህ መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡ ፡

**28. መመሪያውየሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ____________________________ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

# Ministry of Labour & Social Affairs

*Information Sheet on Expatriate Workers*

Instructions: Please PRINT letters in spaces provided.

Photo

Ref no. __

Date: ____________ _

Application Type: ☐ New ☐ Renewal

Basic Data:

Full Name: ________________________________________

Other Name(s): ________________

Sex: ☐ Male ☐ Female Date of Birth: ________________ Nationality: ________________

Marital Status: ☐ Single ☐ Married ☐ Divorced ☐ Widow ☐ Separated

Passport Number: ____________________ Date of Issue: ________________

Visa Number: ____________ Date of Issue: ____________ Visa Type: ☐ Business ☐ Others

Date of Employment: ____________________ Length of Employment: ____________

Basic Salary (In Birr): ________________ Monthly Allowance (In Birr): ____________

Name of the region and district / town where the employee is assigned to work: ________________

Education Data:

Qualification Type: ☐ Certificate ☐ Diploma ☐ Degree ☐ Others (Specify): ____________

Level of Qualification: ☐ Elementary ☐ Junior Secondary ☐ Secondary Level ☐ Secondary Complete

☐ Vocational Level ☐ Vocational Complete ☐ College Level ☐ College Complete

☐ Post Graduate Level ☐ Post Graduate ☐ Non-formal Education

☐ Others ______________________________

Year Completed: ________________ Field of Study: ________________________

Award: ☐ Certificate ☐ Diploma ☐ BA/BSC ☐ MA/MSC ☐ PhD ☐ Other (specify) ____________

Professional Skill: ________________________________________

Years of Work Experience: Starting Date: ________________ End Date: ________________

Type of Occupation: ________________________ Occupation Code: ________________

Current position in the Firm: ________________

Nature of Service: ☐ Employee ☐ Voluntary ☐ Other (specify) ____________

Employer Data:

Organization Name: ______________________________

Address-Region: ____________________ Kebele: ____________________

City/Town: ____________________ Tel.: ____________________

Sub-city/Zone: ____________________ Fax: ____________________

Woreda: ______________________________ P.O.Box: __________

E-mail: ______________________________

Major Activity: ____________________ Activity code: ____________________

Type of Organization: ☐ Private Organization ☐ Governmental ☐ NGO ☐ Religious ☐ Other__________

Industry/Engagement: ☐ Agricultural, Hunting, Forestry & Fishing ☐ Mining & Quarrying ☐ Manufacturing
☐ Electricity, Gas & Water ☐ Construction
☐ Wholesale and Retail Trade ☐ Transport, Storage and Communication
☐ Finance, insurance and Business Services ☐ Community, Social & Personal Services

Number of Ethiopian Employees: ____________ Number of Expatriates: ____________

Investment Permit or Business License Number: ______________________________

..........................................................................................................

Certification

I hereby confirm that all the particulars furnished in this application are free and correct.

Name of the employer or employer's representative______________________________

Title______________________________

Signature: ____________________ Date: ____________________

..........................................................................................................

For Office Use Only:

File Number: ____________________ Application Number: ____________

Support Letter Ref.no: ____________ Signed By: ____________________

Date Signed: ______________________________

Work Permit – Type: ☐ New ☐ Renewal Work Permit Number: ____________________

Issue/Renew Date: ____________ Expiry Date: ____________

Residence Permit – Residence ID: ____________________

Residence ID Issue Date: ____________ ID Expiry Date: ____________

Approved by: ____________________ Signature: ____________________

Date Approved: ____________________